21ኛ ዓመት ቁጥር 9
21th Year No. 9

ባሕር ዳር ጥር 25 ቀን 2008 ዓ.ም
Bahir Dar, 03 February, 2016

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት
# ዝክረ ሕግ
# ZIKRE HIG
## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 26.00 ብር
Unit Price Birr 26.00

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር 238/2008 ዓ.ም**

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የማዕድን ሀብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ**

**Content**

**Proclamation No. 238/2015**

**A Proclamation Issued to Provide for the Establishment of the Mines Resource Development Expansion Agency in the Amhara National Regional State**

## አዋጅ ቁጥር 238/2008 ዓ.ም

## የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የማዕድን ሀብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ

የማዕድን ዘርፍ በአጠቃላይ ለክልሉ ኢኮኖሚያዊ ልማት በተለይም ለስራ ዕድል ፈጠራ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ቢሆንም ተስማሚ በሆነ አደረጃጀት ካለመደገፉ የተነሣ የዘርፉን አስተዋጽኦ በሚጠበቀው ደረጃ ለማሣደግ ይቻል ዘንድ ይህንኑ ገቢራዊ የሚያደርግ ራሱን የቻለ ተቋም መመስረት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

## Proclamation No. 238/2015

## The Amhara National Regional State Mines Resource Development Expansion Agency Establishment Proclamation

WHERE AS, though the contribution of the sector of mining is entirely high for the regional economy development, especially for job opportunity, it is not supported in a suitable organizational structure, enabling to promote the sector's contribution as the expected level, and for the realization of same it is thus found appropriate to establish an autonomous intsitution;

በፌደራሉ መንግስት የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 ዓ.ም /በአዋጅ ቁጥር 816/2006 ዓ.ም እንደተሻሻለ/ አንቀጽ /54/ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የባህላዊ ማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድና ልዩ የአነስተኛ ማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ፣ ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች የግንባታና የኢንዱስትሪ ማዕድናትን በሚመለከት የቅኝት፣ የምርመራና ይዞ የመቆየት ፈቃዶች፣ የአነስተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪ ማዕድናት ማምረት ስራ ፈቃዶች እንዲሁም የአነስተኛና የከፍተኛ ደረጃ የግንባታ ማዕድናት ማምረት ስራ ፈቃዶች፣ ከስትራቴጅካዊ ማዕድናት ውጭ ለሆኑ ማዕድናት ደግሞ የግኝት የምስክር ወረቀት መስጠት የክልል ፈቃድ ሰጭ አካላት ሀላፊነት እንዲሆኑ የተደነገገ በመሆኑ፤

WHERE AS, pursuant to sub-article /1/ of Article /54/ of the Federal Government mining works proclamation No. 678/2010, as revised with a Proclamation No. 816/2013 , the artisanal mining license and various small mining license; the survey, investigation and withholding licensces, concerning to the construction and industrial mining licenses for inland invest tors, the small scale indistrial mining licences, as well as, the small and large scale construction mining licenses, to the excluding mining from strategical mining , also it is stipulated for rendering the certificate of discovery as a responsibility of regional license rendering;

በተመሣሣይ ሁኔታ የከበሩ ማዕድናትን ግብይት ለማስፋፋትና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 651/2001 ዓ.ም መሰረት የነዚህኑ ማዕድናት ዝውውርና የዕደጥበብ ፍቃድም ሆነ የንግድ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስልጣን የክልል መንግስታት በመሆኑ፤

WHERE AS, the mines transfer and the crafting licence, as well as, the certificate of trade competence is authorized to the regional governments, pursuant to the issued Proclamation No.651/2009 to expand and control the precious mines marketing;

በክልሉ ውስጥ ህገ-ወጥ የማዕድናት ምርትና ንግድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ ከመሄዱ የተነሣ ሁኔታውን ለመለወጥ ተገቢውን የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋትና የተፈጥሮ አካባቢ ሣይጎዳ ሃብቱ በቁጠባ ተይዞና ለምቶ የህዝቡ ተጠቃሚነት የሚረጋገጥበትንና ለመጭው ትውልድ የሚተላለፍበትን ሁኔታ ማመቻቸት ጠቃሚ እንደሆነ ስለታመነበት፤

WHERE AS, owing to the fact that illegal minerals exploitation and trading is spreading from time to time, it is believed important to facilitate the condition by putting in place an appropriate controlling mechanism to change the situation in order for the resource to be economically kept and developed without causing damage to the public and transfer same to the coming generation;

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሄራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ /49/ ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

NOW THEREFORE, the Council of Amhara Region, in accordance with the powers vested in it under sub-article 3/1/ of Article /49/ of the Revised National Constitution of the Region, hereby issues this proclamation.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የማዕድን ሀብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 238/2008 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፡-

1) "ማዕድን" ማለት በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ በተፈጥሮ አማካኝነት በመሬት ላይ ወይም በመሬት ውስጥ ፣ በውሃ ውስጥ ወይም ስር የሚገኝ በጂኦሎጅ ሂደት ወይም ሁኔታዎች የተፈጠረ ሆኖ ቀደም ሲል ተቆፍሮ በወጣና ተራፊ የተቆለለ ማዕድን አዘል አፈር ወይም በቀሪ የማዕድን ክምችት ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም ዋጋ ያለው ነገር ሲሆን የሚከተሉትን አይጨምርም፡-

ሀ/ ለመታጠቢያ፣ ለመዝናኛ ወይም ለህክምና አገልግሎት ከሚውል የጂኦተርማል ውሃ ወይም ከውስጡ ማዕድን ለማውጣት ከሚውል እንደ ብራይን ካለ ማዕድን በስተቀር ሌላውን ውሃ፤

ለ/ አግባብ ባለው የፔትሮሊየም ህግ ትርጓሜ ውስጥ የሚካተቱትን የተፈጥሮ ዘይትና ጋዝ፤

ሐ/ ለም አፈርን ወይም ላይኛውን አፈር እና ነዳጅ አዘል አለትን ወይም ነዳጅ አዘል ሽልን፡፡

## PART ONE

## General Provisions

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as "the Mines Resource Development Expansion Agency Establishment Proclamation No. 238/2015.''

### 2. Definition

Unless the context requires otherwise, in this proclamation:

1) "Mines" means any mineral substance of economic value, whether in solid, liquid or gaseous from , occuring naturally on or within the earth or in under water and which was fromed by or subjected to aegological process, and any mineral occuring in residue stockpiles or in residue deposits shall not include the following :

a/ other water except the geothermal water that shall serve for bathing, recreational and medical pirposes or like brines mining that shall serve for producing mining in same;

b/ the natural gas and pertoleum that shall be included, as defined in the relevant petroleum law;

c/ loam soil or top soil and oil rock or oil shale;

2) **"ባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ"** ማለት አብዛኛው ተግባር በእጅ የሚከናወንና ተቀጣሪ ሰራተኛ የማይሳተፍበት ሆኖ በግለሰቦች ወይም በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አማካኝነት የሚከናወን የወርቅ፣ የፕላቲኒየምና ሌሎች የከበሩ ማዕድናት፣ የብረት፣ የጨው፣ የሸክላ አፈርና የመሳሰሉትን ማዕድናት የማምረት ሥራ ነው፤

2) " Artisanal Mining" means a mining operation that is mostly of manual nature and the employeed works do not involve in same , that shall be carried out with regard to individuals or minor and small enterprises of the gold , plateneum; and other precious minerals, metal, salt, the clay soil and other minerals;

3) **"አነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ስራ"** ማለት ከማዕድኑ ስፍራ በዓመት የሚመረተው የማዕድን አዘል አፈርና ድንጋይ መጠን ከሚከተለው የማይበልጥ ማዕድን የማምረት ሥራ ነው፡-

3) " Small Scale Mining Operations" means any mining operation of which the annual run-off mine ore does not exceed from the following:

**ሀ/ ወርቅ፣ ፕላቲኒየም፣ ብርና ሌሎች የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን በሚመለከት፡-**

1. በደለል ላይ ለሚካሄዱ ስራዎች 100,000 ሜትር ኩብ፤
2. በዕንስ ማዕድን ክምችቶች ላይ ለሚካሄዱ ስራዎች 75,000 ቶን፡፡

a/ regarding gold, platinum, silver and other precious and semiprecious minerals:

i. 100,000$m^3$ for placer operation ;

ii. 75,000 tons for primary deposit mining;

**ለ/ እንደ ብረት፣ እርሳስ፣ መዳብና ኒኬል የመሳሰሉ ሜታል ማዕድናትን በሚመለከት፡-**

1. በመሬት ላይ ለሚካሄዱ ስራዎች 150,000 ቶን፤
2. በመሬት ውስጥ ለሚካሄዱ ስራዎች 75,000 ቶን፡፡

b/ regarding metalic minerals such as iron, lead, copper and nickel:

1. 150,000 tons for open pit mining ;
2. 75, 000 tons for under ground mining operation;

**ሐ/ እንደ ካኦሊን፣ ቤንቶናይት፣ ዲያቶማይት፣ ዶሎማይት ኳርትዝና የድንጋይ ከሰል የመሳሰሉ የኢንዱስትሪ ማዕድናትን በሚመለከት** 120,000 ቶን፡፡

c/ 120,000 tons for industrial minerals such as kaolin, bentonite, diatomite, dolomite,quartz and coal;

**መ/ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በሚመለከት፡-**

1. አሸዋ፣ ጠጠር፣ ፑሚስ፣ ኢግኒምብራይት፣ የሸክላ አፈርና የመሳሰሉትን በሚመለከት 80,000 ሜትር ኩብ፤
2. እብነበረድ፣ ግራናይትና የመሳሰሉትን የዳይሜንሽን ድንጋዮች በሚመለከት 10,000 ሜትር ኩብ፡፡

**ሠ/ የጆኦተርማል ክምችትን በሚመለከት፡-**

1. ለመታጠቢያ፣ ለመዝናኛና ለህክምና አገልግሎት የሚውሉትን በሚመለከት 2,000000 ሜትር ኩብ፤
2. ለኢንዱስትሪና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውሉትን በሚመለከት 25 ሜጋዋት ወይም ተመጣጣኝ የሆነ ኃይል ሊሰጥ የሚችል የጆኦተርማል እንፋሎት፡፡

**ረ/ ከድንጋይ ወይም ከብራይን የሚመረቱ የጨው ዓይነቶችን በሚመለከት 14,000 ቶን፡፡**

4) **"ከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ"** ማለት የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮችን የማምረት ሥራን በሚመለከት ካልሆነ በስተቀር ከማዕድኑ ሥፍራ በዓመት የሚነሳው ማዕድን አዘል አፈርና ድንጋይ መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ ስር ከተመለከተው መጠን በላይ የሆኑ ማዕድናትን የማምረት ሥራ ነው፤

5) **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

6) **"ቢሮ"** ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቴክኒክ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ነው፡፡



d/ regarding construction minerals:

1. 80,000 $m^3$ for sand, gravel, pumice, ignimbrite, clay and the like;
2. 10,000 $m^3$ for dimension stones such as marble and granite;

e/ regarding geothermal deposit:

1. 2,000,000 $m^3$ for bathing , recreational and medicinal purpose;
2. 25 mega watt or geothermal steam capable of generating equivalent power for industrial and other purposes;

f/ 14,000 tons for salts extracted from briners;

4) " Large Scale Mining Operations" means any mining operation which produce more than the annual run off mine that indicated in sub-article /3/ of this Article, unless the mining operations of the precious or semi-precious menirals;

5) "Person" means any natural or juridical person;

6) "Bureau" means the amhara National Regional State Techinc vocation and Enterprises Development bureau.

## ክፍል ሁለት

## በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የማዕድን ሀብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ ዓላማ፣ ስልጣንና አወቃቀር

### 3. መቋቋምና ተጠሪነት

1) በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የማዕድን ሀብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ከዚህ በኃላ "ኤጀንሲው" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት አስፈፃሚ መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤
2) የኤጀንሲው ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል፡፡

### 4. ዓላማዎች

ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1) በክልሉ ውስጥ የሚገኙት የማዕድ ሃብቶች ለምተው ለኢኮኖሚው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የሚያበረክቱበትንና ከድህነት ለመውጣት የሚደረገውን ጥረት የሚያግዙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
2) የክልሉ የማዕድን ሃብት ያለአግባብ እንዳይባክን፣ በልማቱ ወቅት አካባቢው እንዳይበከልና እንዳይጐዳ አስፈላጊውን ቁጥጥር ማካሄድ፣ መጠበቅና ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ፡፡

### 5. የኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት

የኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት በባህር ዳር ከተማ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ስፍራዎች ቅርንጫፍ ወይም ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

## PART TWO

## Establishment, Accountability, Objective, Powers and Organizational Structure of the Amhara National Regional State Mines Resource Development Expansion Agency

### 3. Establishment and Accountability

1) The Amhara National Regional State Mines resource development expansion agency, herein after referred to as " the Agency" is hereby established as an autonomous Regional Government Institution, under this proclamation;
2) The Agency shall be accountable to the Bureau.

### 4. Objectives

The Agency shall have the following objectives, pursuant to this proclamation:

1. facilitate the condition to support the effort made to get out of poverty through the development of mineral and resources found in the Region and making same contribute their benefit to the economy;
2. make the necessary control and protection that mineral resources not to be wasted, the environment remains unpolluted and undamaged in time of exploitation , and thereby transfers same to the coming generation.

### 5. Head Office

Head Office of the Agency shall be in Bahir Dar Town, as deemed as necessary, it may establish branch or coordinating offices in another place.

## 6. የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባር

ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) በክልሉ ውስጥ የማዕድን ሀብት ልማት እንዲስፋፋ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በሌሎች እንዲካሄዱ ያደርጋል፣ በነዚሁ ጥናቶች አማካኝነት የክልሉን ዕምቅ የማዕድን ሃብቶች በአይነትና በመጠን ይለያል፤

2) በክልሉ ውስጥ የስነ-ምድር ጥናትና ምርምሮችን ያካሒዳል ወይም እነዚህኑ የመሳሰሉ ጥናትና ምርምሮች በማካሔድ ረገድ አግባብ ካላቸው የፌዴራሉ መንግስት አካላት ጋር ተባብሮ ይሰራል፤

3) የግል ባለሃብቶች በማዕድን ሀብት ልማት ስራዎች በስፋት እንዲሣተፉ ያነሳሳል፣ የተለያዩ የፕሮሞሽን ስራዎችን በማከናወን ያበረታታል፤

4) ዘረፉ ለላቀ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ውጤታማ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት አደረጃጀቱን በማሻሻልና አቅሙን በመገንባት ረገድ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል፤

5) ማዕድንን አስመክልቶ በሀገሪቱ የወጡ ህጐች በክልሉ ውስጥ በስራ ላይ ስለመዋላቸው ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

6) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በባህላዊ፣ በአነስተኛ፣ በልዩ አነስተኛና በከፍተኛ ደረጃ የሚካሄድን የማዕድን ሀብት ፍለጋ፣ ምርመራ ፣ግኝት፣ ምርትና ይዞ የመቆየት ፈቃዶችን ይሰጣል፣ ያድሣል፣ ይሠርዛል፤

7) በክልሉ ውስጥ የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ማዕድናትን አመራረት፣ ግብይትና አስተዳደር



## 6. Powers and Duties of the Agency

The agency shall have the following particular powers and duties, pursuant to this proclamation:

1) conduct studies so as to expand mineral resource development in the region; and cause to be undertaken by others; separate the regional pentiful mineral resources with kind and amount with regard to these studies;

2) Perform in coordination with the appropiate Federal Government bodies in view of conducting the geological study and researches of geology in the Region;

3) initiate and encourage through undertaking various promotion activities that private investors take part broadly in mineral resource development activities;

4) put an appropriate effort with regard to improving the organization of the sector and building its capacity so that it makes effective contribution for higher economic growth;

5) ensure and supervise that laws promulgated in the country concerning to minerals are implemented in the region;

6) issue, renew and cancel, in cooperation with the pertinent bodies , license of mineral resources' exploitation, investigation, finding, and production exploitation being undertaken traditionally small, special small and in large scale;

7) follow up and supervise the precious or semiprecious minerals' productivity, marketing and administration in the region;

ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

8) ባህላዊና አነስተኛ የማዕድን ማምረት ስራዎችን ይደግፋል፣ በክልሉ ውስጥ ዜጎች በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ተደራጅተው በዚሁ ተግባር ላይ ለመሠማራት የሚያስችል የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ያበረታታል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

9) ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ የሚከናወን ማናቸውም የማዕድናት ምርትና ዝውውር እንዲገታ አስፈላጊውን የቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፣ ይቆጣጠራል፣ በህገ-ወጥ መንገድ ተይዘው የተገኙ ማዕድናት በአግባቡ ተጠብቀው ህጋዊ ውሣኔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

10) በማዕድን ሃብት ልማት ሂደት የሚገኝ የሮያልቲ፣ የመሬት ኪራይና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶች ክፍያዎችን ይሰበስባል፤

11) ማዕድንን የሚመለከቱ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

12) አግባብ ባላቸው የማዕድን ሀብት ልማት ማስፋፊያ ህጎች ከተፈቀደው ወሰን ሣያልፍ በባለ አክሲዎንነትሊሳተፍ ይችላል፤

13) የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውሎችን ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሣል፣ ይከሰሳል፤

14) ዓማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

8) support traditional and small scale mineral exploitation works, encourage the realization of job opportunity that shall enable citizens to be organized with micro and small institutions and apply in same of the region; render license and supervise thereof;

9) put in place the necessary controlling system and thereby supervise to restrain any illegal exploitation of products and transfering activity of mineral resources; cause minerals found illegally seized properly kept and get a verdict thereof;

10) collect charges of royalty and other related services gained in the process pf exploiting mineral resources;

11) collect, analyze and organize informarion relating to minerals; and distribute to beneficiaries;

12) may pariticipate in share not go beyond the authorized amount based on the appropriate mining resource development expansion laws;

13) own property, inter into contracts, sue and be sued;

14) carry out other legal functions necessary to achieve its objectives.

## 7. ድርጅታዊ አቋም

ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

1) በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾሙ ዋናና ምክትል ዳይሬክተሮች፤
2) ለስራው የሚያስፈልጉ ሙያተኞችና ሌሎች ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች።

## 8. የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር

1) ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ስራ አስፈፃሚ በመሆን በዚህ አዋጅ አንቀፅ /6/ ስር ለኤጀንሲው የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ያውላል፤
2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ ስር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ/ የኤጀንሲውን የዕለት ተዕለት ስራ በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

ለ/ በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የኤጀንሲውን ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሳድጋል፣ ያሰናብታል፤

ሐ/ የኤጀንሲውን የስራ ፕሮግራምና የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ በቢሮው አማካኝነት ለክልሉ መንግስት ያቀርባል፣ ሲፀድቅለትም በተግባር ላይ ያውላል፤

መ/ በኤጀንሲው ስም የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፤

ሠ/ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ/ የስራ እንቅስቃሴውን አስመልክቶ ለቢሮውና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ወቅታዊ ሪፖርቶችን ያቀርባል፤

## 7. Organizational Structure

The Agency shall have the following bodies, pursuant to this proclamation:

1) General and Vice Director appointed with the Head of the Regon;
2) Professionals and other supporting staffs, necessary for the work.

## 8. Powers and Duties of the General Director

1) The General Director, being the main executive body of the agency shall implement the agency's powers and duties rendered, under Article/6/ of this proclamation;
2) Without prejudice to the General provision stipulated under sub-article /1/ of this Article, the General Director:

a/ direct over and coordinate the agency's day-to-day activities;

b/ recruit, administer, promote and fire the agency's employees, pursuant to the regional civil service laws;

c/ prepare and submit the agency's work program and the implementable budget draft to the Regional Government with regard to the Bureau; implement same upon approval;

d/ open book account and circulate money on behalf of the agency;

e/ represent the agency in its dealings with other third parties;

f/ submit periodic reports to the Bureau and the Regional Government Council, concerning to its activities;

ሰ/ ለኤጀንሲው የስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ከስልጣንና ተግባራቱ ከፊሉን ለኤጀንሲው የበታች ስራ ሀላፊዎችና ሌሎች ሰራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

g/ may transfer part of its powers and duties with delegation to the subordinate heads and other employees of the agency with the necessity amount of efficiency of the agency.

## 9. ስለ ምክትል ዳይሬክተሩ

የኤጀንሲው ምክትል ዳይሬክተር ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተሩ ሆኖ፡-

1) በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤
2) ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ወይም ስራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሰራል፡፡

## 9. Vice Director

The Vice Director of the agency, being accountable to the Feneral Director, shall:

1. carry out activities that shall be selected and rendered to him by the General Director;
2. act on behalf of him, where in the absence or inability of the General Director to carry out his activities.

# ክፍል ሶስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

# PART THREE

# MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 10. ስለ በጀት

የኤጀንሲው በጀት በክልሉ መንግስት ይመደባል፡፡

## 10. Budget

Budget of the agency shall be allocated with the Regional Government.

## 11. ስለ ሂሣብ መዛግብት አያያዝና ኦዲት

1) ኤጀንሲው ትክክለኛ የሆኑና የተሟሉ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል፤
2) የኤጀንሲው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ወይም እርሱ በሚወክለው አካል በየጊዜው ይመረመራሉ፡፡

## 11. Recording and Audit of the Book Accounts

1) The agency shall keep the accurate and complete book accounts;
2) The books of account and other financial or property related documents belonging to the agency shall be audited by the Office of the Auditor General or a body delegated with him on periodic basis.

## 12. ስለ ተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

1) በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የማዕድንና የገጠር ኢነርጅ ሀብት ልማት ማስፋፊያ ጽ/ቤትን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 100/1996 ዓ.ም ተሽሮ የማዕድን ሀብት ልማትና ቁጥጥር ስራዎችን በሚመለከት በዚህ አዋጅ ተተክቷል፤

## 12. Repealed and Inapplicable Laws

1) An Issued Proclamation No. 100/2004 to establish the Amhara National Regional Sate of the Mines and Rural Energy Resource Development Expansion Office is repealed and replaced with this proclamation, concerning to the Mines Resource Development and supervision works;

2) ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

2) Any law, regulation, directives or customary practice inconsistent with this proclamation shall not be applicable on matters provided in this proclamation.

## 13. መብቶችና ግዴታዎችን ስለማስተላልፍ

የክልሉን ማዕድን ሀብት ልማትና ቁጥጥር ስራዎች አስመልክቶ ቀደም ሲል በአዋጅ ቁጥር 100/1996 ዓ.ም ለተቋቋመው የማዕድንና የገጠር ኢነርጅ ሀብት ልማት ማስፋፊያ ጽ/ቤት ተሰጥተው የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ አዲስ ወደ ተቋቋመው የክልሉ ማዕድን ሀብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ተላልፈዋል፡፡

## 13. Transfer of Rights and Obligations

The rendered rights and obligations to the established Mines and Rural Energy Resource Development Expansion Office previously with a proclamation No. 100/2004 concerning to the Regional Mines Resource Development and supervision works, have been transfered to the newly established Regional Mines Resource Development Expansion Agency.

## 14. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1) የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፤

2) ቢሮው ይህንን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚረዱትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 14. Power to Issue Regulation and Directives

1) The Regional Government Council may issue regulations necessary for the full implementation of this proclamation provisions;

2) The Bureau may issue particular directirves necessary for the full implementation of this proclamation and regulations to be issued, pursuant to this proclamation.

## 15. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## 15. Effective Date

This proclamation shall come into force as of the official of its publication in the Zikre-Hig Gazzettee of the Regional State.

**ባህር ዳር**
**ጥር 25 ቀን 2008 ዓ.ም**
**ገዱ አንዳርጋቸው**
**የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዚዳንት**

**Done at Bahir Dar,**
**This 3rd Day of February, 2016**
**Gedu Andargachew**
**President of the Amhara National Region**